ማስታወሻ

ቀጥለው ከታች የሠፈሩ የቁርአን አንቀጾች ተሰፋ ሰጭ፣ ወደ ራሳችን እንድንመለከት የሚያደርጉ እና አበረታች መልዕክቶችን የያዙ ናቸው። ትርጉሙ ቃል በቃል አይደለም። ቁርአን ውስጥ በየትኛው ምዕራፍና አንቀጽ እንደሚገኙ ፊልጉና አስተንትኑ። አላህ ተጠቃሚዎች ያድርገን።

1- ለጌታህ ፍርድ ታገስ፤ በዕይታችን ሥር ነህና፤

2- አላህ ከዚህም ሆነ ከያንዳንዱ ጭንቀት ያወጣችኋል፤

3- ጌታችን ሆይ! የማንችለውን ነገር አታሸክመን፤

4- ጌታችሁ ስለናንተ ያውቃል፤

5- ሳቀችም፤ በኢስሓቅም አበሰርናት፤

6- "ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ጥራት ይገባህ" አለና በጨለማዎች ውስጥ ተጣራ፤ ምላሽ ሠጠነው፤ ከጭንቀትም አዳንነው። በዚሁ መልኩ አማኞችን እናድናለን።

7- በርግጥ ጌታዬ ዱዓን ይሰማል፤

8- አላህም ከችግር በኋላ ገርን ያመጣል፤

9- አላህ ዘንድ ያለው በላጭም ዘላቂም ነው፤

10- የሳትከ ሆነህ አገኘህ፣ መራህም፤

11- አላህን የሚፈራ መውጫን ያበጅለታል፤ ካላሰበውም በኩልም ይለግሰዋል፤ በአላህ የተመካ እርሱ በቂው ነው፤ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፤ አላህ ለሁሉም ነገር የተወሰነ ጊዜን አድርጓል፤

12- አላህ ከዚያ በኋላ አንድን ነገር ያስከስት እንደሆነ አታውቅም፤

13- ጌታውን ተጣራ... ምላሽም ሠጠነው፤

14- ባሮቸህ ስለኔ በጠየቁህ ጊዜ "እኔ ቅርብ ነኝ፣ በለመነኝ ጊዜ ለለማኝን ልመና ምላሽ እሠጣለሁ፤ ለኔ ጥሪ ምላሽ ይስጡ፤ በኔ ይመኑ፣ ይቀኑ ዘንድ።"

ከማን ጋር መሆን እንዳለባችሁና እንደሌለባችሁ

፩- ከአላህ ጋር ሁኑ

ከአላህ ጋር የሆነን ሰው አላህ ከሱ ጋር ይሆናል። ይጠብቀዋል፤ ይረዳዋል፤ ይደርስለታል። ከአላህ ጋር መሆን ማለት የአላህን ውዴታ ለማግኘት ዕድሜ ልክ መዳከር ማለት ነው። አላህ ባዘዘው ነገር መሥራት፣ ከከለከለው መከከልከል፣ እሱ ከሚጠላው ነገር መራቅ፣ የሚወደውን መፈፀም ነው ከአላህ ጋር መኖር። አላህ መልካም ነው መልካም ነገሮችንም ይወዳል። በመልካም ነገሮች ሁሉ በተለይ እሱ ግዴታ ባደረጋቸው ነገሮች ወደ አላህ የሚቃረቡትን አብዝቶ ይወዳቸዋል። የቀረቡትንም የበለጠ ያቀርባል። ከአላህ ጋር መኖር -በምላስ እሱን ማወደስ፣ በቀልብ ከሱ ጋር መተሳሰር፣ በሃሳብ ከሱ አለመለየት ነው። ከአላህ ጋር መሆን የደስታ ምንጭ፣ የሐሴት ሁሉ መሠረት ነው።

2- ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሁኑ

አማኝ የአላህን መልዕክተኛ ከማንኛውም ሰው ከነፍሱም በላይ አብልጦ ሊወዳቸው ይገባል። ከዝንባሌውም በላይ የርሳቸውን ዝንባሌ መከተል ይኖርበታል። ከርሳቸው ጋር መሆን ስንል ከርሳቸው የሆነውን ነገር ሁሉ መውደድ ነው። ይዘው የመጡትን እስልምና ማመንና መቀበል፣ ያዘዙትን መፈፀም፣ ከከለከሉት መከከልከል፣ አላህንም እርሳቸው ባሳዩት መንገድ ማምለክ ነው። ከአላህ መልዕክተኛ ጋር መሆን ሲባል ፈለጋቸውን መከተል፣ አስተምህሯቸውን መያዝ ነው። የአላህን መልዕክተኛ መታዘዝ አላህን መታዘዝ ነው። እርሳቸውን መውደድ አላህን መውደድ ነው።

3- ከቁርአን እና ሐዲሥ ጋር መሆን

ቁርአን የፈጠረን አምላክ የአላህ (ሱ.ወ.) ቃል ነው። ከቃሉ ጋር መሆን ከአላህ ጋር መሆን ነው። ቃሉን ለነፍስም ለአጥንትም ጤና ነው። ቁርአንን ማንበብ ምንዳው የበዛ አምልኮ ነው። አዘውትሮ ማንበብ ከአላህ ጋር መሆን ነው። ሐዲሥ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ንግግርና አስተምህሮ ነው። እርሳቸው አስተምህሮውን ያመጡት ከራሳቸው አይደለም። አላህ ነው የገለጠላቸው። ከሐዲሥ ጋር መሆን ከአላህ መልዕክተኛ፣ ብሎም ከአላህ ጋር መሆን ነው። ንግግራቸውን መውደድ እርሳቸውን መውደድ ነው።

መልካም የተባለ አስተምህሮ ሁሉ ቁርአንና ሐዲሥ ውስጥ አለ። እነርሱን በተግባር መኖር ከአላህና ከመልዕከተኛው ጋር መኖር ነው።

4- ከአላህ ባሮች ጋር ሁኑ

የአላህ ባሮች የአላህ ወዳጆች ናቸው። አላህን ይወዳሉ፤ አላህም ይወዳቸዋል። ከአላህ ወዳጆች ጋር መሆን ሳለት ባሮቹን መውደድ፣ ወደነርሱ መጠጋት፣ ከነርሱ ጋር መወዳጀትና መቀማመጥ ነው። የአላህ ባሮች የተጠቁ እንደሆነ መከላከል፣ የተከፉ እንደሆነ ማጽናናት፣ ያዘኑ እንደሆነ ማስደሰት... ከባሮቹ ጋር መሆን ነው። ከነርሱ ጋር መሆን ለመልካም ሥራ መንገድ ነው። አላህ እና መልዕከተኛው ዘንድም የሚያሰወድድ ነው።

5- ከደስተኞች ጋር ሁኑ

ደስተኛ ሰው ማለት አላህን የሚወድ ሰው ነው ብዬ አስባለሁ። ደስተኛ የሆነውም በምክንያት ነው። አላህ የወደደለትን ስለወደደ፣ በቀዷና ቀደር ስላመነ፣ የአላህን ከፍፍል ስላመነ ነው ደስተኛ ሊሆን የቻለው። ደስተኞች በዚህች ምድር ላይ አላህ ቀድሞውኑ የፃፈላቸውን ሕይወት እየኖሩ እንዳሉ ያውቃሉ፤ ሁሉም ነገር ከልኩ እንደማያልፍ ይገነዘባሉ። ሰው ሀብት ሞልቶ ስለተረፈው፣ አብዝቶ ስለተማረ ሳይደለም ደስተኛ የሚሆነው። የሙእሚን ደስታ ምንጩ ሣግኘት አሊያም ማጣት አይደለም። የደስታ መገኛዋ ቀልብ ውስጥ ነው። ስንት ድሆች አሉ ከሃብታሞች በላይ ደስተኛ የሆኑ። ስንት ሃብታሞች አሉ ሞልቶ ተርፏቸው የብስጭት ኑሮ የሚኖሩ። ከደስተኞች ጋር ሁኑ። ደስታን ይለግሷችኋል፤ ሐዘንን ያባርሩላችኋል፤ ችግርን ያስረሷችኋል።

6- ከተሰፈኞች ጋር ሁኑ

ተስፋ ባይኖር ኖሮ ሕይወትም አታጓጓም ነበር። ሙእሚን ተስፈኛ ነው። ተስፋውም በማንም ሳይሆን በአላህ ላይ ነው። ተስፋው ሃብታምም፣ ባለሥልጣንም አይደለም። ለያስቀጥረው ብሎ ኢድራሻውን የወሰደውም አይደለም። ትልቁ ተስፋው አላህ ነው። አላህ ወደተሻለ ነገር እንደሚያሻግረው ያስባል፤ የተሻለ ነገር እንደሚሠጠውም ያምናል። የነገው ቀኑ ከዛሬው እንደሚሻል፤ የወደፊቱ ካለፈው እንደሚበልጥ ተስፋ ያደርጋል። በአጁ ካለው በላይ አላህ ዘንድ ያለውን ያምናል። ጥሩ ተስፋ ጥሩ ሰላም

አርግዟል። ውስጥን ያረጋጋል፤ መንፈስን ያድሳል፤ ሕይወትን ያሳምራል። ሰላማዊ ሕይወት መምራት ከፈለጋችሁ ከጨለምተኞች ራቁ፤ ከብርሃን ፈንጣቂዎች ተጠጉ፤ ከመልካም አበሳሪዎች ተወዳጁ። ፊት ለፊታችሁ መልካም እንደሆነ የሚነግራችሁን፣ ጓደኛ አድርጉ። ተስፋ የሚሠጣችሁ ሰው ይወዳችኋል፤ ሁሌም በጎ ነገር እንደሚገጥማችሁ ይነግራችኋል። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ህልም እንኳን ስታዩ ለምትወዱት ሰው ንገሩ ነው ያሉት፤ እሱ በመልካም ነገር ይፈታላችኋል።

7- ከጥሩ አሳቢዎችና ተጠራጣሪዎች ጋር ሁኑ

የጥርጣሬ ብዙ አጂ ወንጀል ነው፤ አሊያም ወንጀል ላይ ይጥላል። በሁሉም ነገር ውስጥ ከፋት ብቻ የሚሸታቸው ሰዎች አሉ። የሚታየውን አዎንታዊውን ነገር ትተው በአሉታዊው ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ሁሉን ነገር ይጠራጠራሉ። ከሁሉ ነገር አንባር ያመነታሉ። ከመልካም ሰው ውስጥ መጥፎ ጎን ይፈትሻሉ። በሰው ላይ የተሸሙ ይመስል የሰውን ገመና ይሰልላሉ። በጎ ሥራ እንዳይሠራ ውሸንብር ይነዛሉ፤ ልቦናቸው በጥርጣሬ ስለተሞላ ጠርጥረው ያስጠረጥራሉ። በትንሽ በትልቁ ተጠራጣሪ ከሆነ፣ መልካም ነገር ከማይታየው ሰው ጋር አትቀመጡ፤ የሚናገረውን አትስሙ፤ የሚጽፈውንም አታንብቡ። ከጉዟችሁ ይገታችኋል፣ ከስኬት መንገድ ያስቀራችኋል። የሽሆችን፣ የሀሳሞችን፣ የኡስታዞችንና የምእመናን ንግግር በአሉታዊ ጎኑ ብቻ የሚረዳ፣ ውስጡን በርብሮ እንከኖቹን አንድ ሁለት እያለ የሚቆጥር፤ እሱ ሰው መልካም አይደለም። ነገር ሰንጣቂ ራሱን ሰላም ነስቶ ሰውንም ሰላም ይነሳል። ራሱ ኃጢኣት ላይ ወድቆ ሌሎችንም ጥፋት ላይ ይጥላል። እናም ራቁት መራቅ ይበጃል።

8- አካባጅ ካልሆነ /ቀለል ካለ/ ሰው ጋር ሁኑ

ሙአሚን ቀላል ነው፤ ሙአሚን ተግባቢ ነው፤ ሙአሚን ተጫዋች ነው፤ ሙአሚን በቀላሉ የሚለመድ ነው፤ አይከብድም አያካብድም። ከሌላው ሰው የተለየ ደረጃና ከብር አለኝ ብሎ አያስብም፤ የተለየ ቦታ አለኝ ብሎ አይመፃደቅም። ደረጃውን ረስቶ የሚኖር፣ ትልቅ ሥልጣኑ ትዝ የማይለው፣ ለዚህም ለዚያም ፈገግታውን የሚለግስ፣ ከድሃ ሃብታሙ ግብግ የማይቀር፣ አለኝ ብሎ የማይኮራ፣ በበቃው ቦታ የሚቀመጥ፣ ከሠራተኞቹ ጋር የሚበላ... የዚህ ዓይነቱ ነው ጥሩ ሙስሊም ማለት።

9- ከቅኖች ጋር ሁኑ

ሙስሊም ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ ይወዳል፤ እሱ ያገኘውን ሌላው ቢያገኝ ይመኛል፣ መልካምነቱ ለሁሉም ነው። መልካም ነገር ከሚያስብላችሁ ሰው ጋር ሁኑ፤ ስታጠፉ ከሚገስፃችሁ፣ ስትጠፉ ከሚመክራችሁ፣ ስትጎዱ ከሚያስብላችሁ ጋር ሁኑ።

10- ተቺዎችን ራቁ

ገና ሲፈጥራቸው ለትችት ብቻ የተፈጠሩ የሚመስሉ ሰዎች አሉ። ሥራ የላቸውም፤ ሥራቸው ትችት ብቻ ነው። ሩቅ ሆነው መታዘብና መመልከት ብቻ፤ አይሠሩም አያሠሩም። ሃሳብም ሆነ ተግባር የላቸውም። ማናናቅ፣ ማሰደንገጥና ማጣጣል ብቻ ነው ሥራቸው። በያንዳንዱ ነገር ላይ አቃቂር ያወጣሉ፤ የሰዎችን ሃሳብም ሆነ ሥራ ይንቃሉ፤ የሰውን ሩጫና ጥረት ያጣጥላሉ። መሪንም፣ ሠራተኛውንም፣ ዓሊሙንም፣ ጃሂሉንም አይተዉም። እስቲ አንተ ገብተህበት ሥራ ብትላቸው አይሠሩም።

ከነሱ ጋር ጓደኛ አትሁን ወዳጄ። ሥራ ያስፈቱሃል። ከጉዞህ ያቆሙሃል። ትችታቸው ቢወርድብህ ባህሪያቸው ነውና አይግረምህ። ምንም ብትል አታሳምናቸውምና አነርሱን ለማሳመን አትድከም፤ በነርሱ ለመወደድና ተቀባይነት ለማግኘት ብለህ አትድከም፣ ለነርሱ ብለህ ከአቋምህ አትውረድ፣ ከነርሱ ለመታረቅ ብለህ ከመንገድህ አትውጣ። ለሰው ብለህ ኑሮህን አታበላሽ፤ ከአላህ ጋር ያለህንም ግንኙነት አታበላሽ። ለሰው ብለህ ስትሠራ፤ ሰው እንዳያጠቃኝ እንዳያሳጣኝ ብለህ ስትሠራ አላህንም ሰውንም ታጣለህ። እነሱ ምናቸውም አይጨበጥም። ዛሬ ሰፊ ልብስ ያለብሱሃል፤ ነገ ጠባብ ልብስ ይደርቡሃል።